# የመንግስት ድጎማዎች: ይህ በእኔ ላይ ተግባራዊ ይሆናል?

UPDATED ፌብሩዋሪ 2020

## ለራስዎ እና ለቤተሰብዎ ትክክለኛውን ምርጫ ይምረጡ



**የመንግስት ድጎማ በሁሉም ስደተኞች ላይ ላይተገበር ይችላል።** እያንዳንዱ ቤተሰብ ልዩ ሲሆን ለእርሶ ቤተሰብ ድጋፍ የሚያደርጉ ፕሮግራሞች በፖሊሲው ላይ የሚደረገው አዲሱ ለውጥ አካል ላይሆኑ ይችላሉ። **ለእርሶ ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ብዙ ሰዎች እና ድርጅቶች አሉ።** በዚህ ጉዳይ ላይ ልምድ ያለው የስደት ጠበቃ ለእርሶ ሁኔታ የሚሆነውን አይቶ ምክር ሊሰጥዎ ይችላል። አካባቢያዊ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እርዳታ እና ህጋዊ ድጋፍ ሊያደርጉልዎ ይችላሉ።

## የመንግስት ድጎማ ምንድን ነው?

አንዳንድ ለግሪን ካርድ (ህጋዊ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ) ወይም አሜርካን ሀገር ውሰጥ ለመግባት ቪዛ የሚያመለክቱ ሰዎች የ "መንግስት ድጎማ" ፈተናን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል – ይህም አንድ ሰው ወደፊት የመንግስት ድጎማዎችን መጠቀም ያስፈልገው ይሆን አይሆን የሚመለክት ነው። ይህንን ውሳኔ በመወሰን ሂደት ውስጥ፣ የስደት መኮንኖች የአንድን ሰው ሙሉ ሁኔታ የሚገመግሙ ሲሆን ይህም እድሜ፣ ገቢ፣ ጤና፣ ትምህርት ወይም ክህሎት (የእንግሊዘኛ ቋንቋ ክህሎትን ጨምሮ)፣ ሲሆን ከዚህ ውስጪ ድጋፍ የሚያደርግላቸውን አካል ቃለ መሀላ ወይም ውል ጨምሮ ነው። በተጨማሪም አንድ ሰው አንዳንድ የመንግስኤ ፕሮግራሞችን ተጠቅሟል ወይስ አልተጠቀመም የሚለውንም ይጨምራል።

**የ DHS አዲሱ የመንግስት ድጎማ ፈተና የሚከተለውን ከግምት ውስጥ ያስገባል:**

- የተጨማሪ ምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP፣ "EBT" ወይም "የምግብ ማህተሞች")
- ፌደራል የመንግስት ቤት እና ክፍል 8 ድጋፍ
- ሜዲኬድ (ድንገተኛ ጉዳትን ሳያካትት፣ እድሜያለቸው ከ 21 በታች የሆኑ ልጆችን፣ እርጉዝ የሆኑ ሴቶችን እና አዳዲስ እናቶችን አያካትትም)
- የካሽ ድጋፍ ፕሮግራሞች (እንደ SSI፣ TANF፣ ጠቅላላ ድጋፍ)

አብዛኛዎቹ አዲሱ ህግ የሚመለከታቸው ሰዎች ከላይ ላለው ጥቅም ብቁዎች አይደሉም። ከላይ ያልተጠቀሱ አገልግሎቶች በመንግስት ድጎማ ፈተና ውስጥ ይቆጠራል፤ ይህም WIC፣ CHIP፣ የትምህርት ቤት ምሳ፣ የምግብ ባንክ፣ መጠለያዎችን፣ የክልል ወይም አካባቢያዊ እንክብካቤ ፕሮግራሞችን እና ሌሎችም ብዙ ነገሮችን የሚያካትት ነው።

# የመንግስት ድጎማዎች: ይህ በእኔ ላይ ተግባራዊ ይሆናል?

UPDATED ፌብሩዋሪ 2020



**እርሶ እና የእርሶ ቤተሰብ አባላት የአሜሪካ (U.S.) ዜግነት አላቹ?**
የህዝብ ሸክም እርስዎን አይመለከትም። እርስዎ ብቁ ለሆኑባቸው ፕሮግራሞች መመዝገብዎን መቀጠል አለብዎት።






**እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባላት ቀድሞውኑ የመኖሪያ ፈቃድ አላችሁ?**
የመኖርያ ፈቃድዎን ሲያድሱ ወይም የአሜሪካ (U.S.) ዜግነት ለማግኘት ሲያመለክቱ የሕዝብ ሸክም (Public Charge) ተፈጻሚ አይሆንም። ዜጋ:: ሆኖም ከስድስት ወር ለሚበልጥ ጊዜ አገሩን ለቀው ለመውጣት ካቀዱ ከኤሚግሬሽን ጠበቃ ጋር መነጋገሩ ጥሩ ሀሳብ ነው ።






**ለሚከተሉት የሙብት ሁኔታዎች ያመለክታሉ ወይም አለዎት? TPS፣ U፣ ወይም T ቪዛ፣ የጥገኝነት ወይም የስደተኝነት፣ ወይም ልዩ የወጣቶች የስደተኝነት ደረጃ** የሕዝብ ሸክም (Public Charge) ምርመራው እዚህ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውስጥ ላመለከቱ ሰዎች አይሰራም። ቀድሞውኑ እነዚህ የኢሚግሬሽን ሁኔታዎች ካለዎት ወይም ለማመልከት በሂደት ላይ ከሆኑ፣ ብቁ የሆኑባቸውን ማንኛውንም የመንግስት ፕሮግራሞችን መጠቀምዎን መቀጠል ይችላሉ።






**ቤተ ሰብ ላይ የተመሰረተ ግሪንካርድ ለማመልከት አቅደዋል?**
የመንግስት ድጎማ ፈተና በአርሶ ላይ ሊተገበር ይችላል። አሜርካን ሀገር ውስጥ የማስተካከያ ቃለ መጠይቅ ላላቸው ሰዎች በመንግስት ፕሮግራሞች የመጀመሪያ ገጽ ላይ ያሉ ፕሮግራሞች ብቻ በመንግስድ ድጎማ ፈተና ውስጥ የሚተገበሩ ይሆናል። እድሜዎ፣ ገቢዎ፣ ጤናዎ፣ የትምህርት ክህሎትዎ፣ የቤተሰብ ሁኔታዎ እና የስፖንሰርዎ የድጋፍ ቃለ መሀላ ከግምት ውስጥ የሚገባ ይሆናል። ማንኛውንም ውሳኔ ከማድረግዎ በፊት በጉዳይዎ ላይ ምክር ለማግኘት ከባለሙያ ጋር መነጋገር አለብዎት። በአካባቢዎ ለሚገኙ ነፃ ወይም ቅናሽ የዋጋ አማራጮች፣ የሚከተለውን ይጎብኙ: https://www.immigrationadvocates.org/nonprofit/legaldirectory/



PROTECTING IMMIGRANT FAMILIES

**FOR MORE RESOURCES GO TO WWW.PROTECTINGIMMIGRANTFAMILIES.ORG**